הרשות להגנת הפרטיות
THE PRIVACY PROTECTION AUTHORITY
سلطة حماية الخصوصية

משרד המשפטים
MINISTRY OF JUSTICE | وزارة العدل

105
Child Online Protection Bureau
www.105.gov.il

# በርቀት በምትማሩበት ጊዜ የግል ምስጢሮችን መጠበቅ ያስፈልጋችኋል



ለኮምፒዩቴራችሁ እና ለምትጠቀሙባቸው ለሩቅ ትምህርት “አፕሊኬሽኖች”) በጣም ጠንካራ የሆነ “ፓስወርድ” (“ሲስማ”) ተጠቀሙ



በምትጠቀሙበት ኮምፒዩቴር ያለው “አንቲቫይረስ” ወቅታዊ እንዲሆን አድርጉ



የቤታችሁ “ኔትወርክ” (“ሬሼት”) ወቅታዊ በሆነ Firewall አማካይነት እንደሚጠበቅ አረጋግጡ። ምክንያቱም የቤታችሁ Wi-Fi በ“ፓስወርድ” አማካይነት በደንብ ስለሚጠበቅ ነው



የኮምፒዩቴራችሁን ካሜራ በማትጠቀሙበት ጊዜ በመሸፈኛ ወይም በማጣበቂያ ሸፍኑት



አስፈላጊ እስካልሆነ በስተቀር የግላችሁን ዝርዝር መረጃዎች ግልጽ አታድርጉ። በምዝገባ ጊዜና “አፕሊኬሽኖቹን” በምትጠቀሙበት ጊዜ አስፈላጊ የሆኑ አነስተኛ ዝርዝሮችን ብቻ ጥቀሱ



በቡድናችሁ ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ተሳታፊዎችን ዝርዝር መረጃዎችን ለመጠበቅ ሞክሩ። የሌሎች ተሳታፊዎችን ግላዊ መረጃዎችን አትጠብቁ (“ሴቭ” አታድርጉ)። የኮምፒዩቴር ስክሪን ፎቶ አታንሡ፣ እንደዚሁም እነዚህን መረጃዎች አታስተላልፉ



“አፕሊኬሽኑን” በደንብ አጥኑ እንደዚሁም የአፕሊኬሽኑን የተለያዩ ክፍሎች በደንብተማሩ። እንደዚሁም ግላዊ መረጃዎችን ጠብቁ



ለውይይት የምታቀርቡት ግልጽ የሆነ መረጃ/ይዘት ሲሆን ለሌሎች በአፕሊኬሽኑ ለሚጠቀሙ አካላት ቢቀርብ ችግር አይፈጥርም ብላችሁ የምታምኑበት ነው። ሌሎች እንዳያውቁት የምትፈልጉት ማቴሪያል ካላችሁ በግል ኢ-ሜይል ወይም በሌላ መንገድ ላኩ



የናንተ ቡድን አባል ያልሆነና የማታውቁት ግለሰብ ለግላዊ “ቻት” ከጋበዛችሁ መልስ እንዳትሰጡ



ትምህርቱን በምትማሩበት ጊዜ ወደሚላክላችሁና ወደማታውቁት ድረ-ገጾች አትግቡ። የምትገቡት ሕጋዊ የሆኑ አካላት ወደሚልኩላችሁ ድረ-ገጾች ብቻ ሲሆን እነዚህም ድረ-ገጾች ከትምህርታችሁ ክፍል ውስጥ አንድ ከሆኑ ነው



## ችግር አጋጥሟችኋል?

እንደዚያ ከሆነ ወላጆቻችሁ፣ የውይይቱ አመራሮች ወይም የትምህርቱ ሕጋዊ ወኪል የሆኑትን በችግራችሁ ላይ አሳትፏቸው

አካለ መጠን ያላደረሱ ልጆች የኢንቴርኔት ጥቃት በሚደርስባቸው ጊዜ ለስልክ ቁጥር 105 በማንኛውም ጊዜ መደወል ይቻላል

የግል ምስጢር ላይ ጉዳት ደርሷል የሚል ወይም የግል ዝርዝር መረጃ ያላግባብ ጥቅም ላይ ውሏል የሚል ጥርጣሬ ካለ ለግል ዝርዝሮች መከላከያ ባለሥልጣን በድረ ገጽ www.ppa.justice.gov.il አማካይነት አመልክቱ

Ministry of Public Security | Israel Police | Ministry of Education | Ministry of Labor & Social Affairs | Ministry of Health